በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ
የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው:: እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንንያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታኳ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበ□ል::

- □□ቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በህክምና ትምህርት ኮሌጅ ለጠቅላላ እና እስፔሻሊስት ሀኪሞች የቶፐአፕና ክሊኒካል አበል ክፍያ እንዲከፈል በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በተወሰነው መሰረት ከሃምሌ/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 እና በ2008 በጀት ዓመት ያልተከፈለውን ጨምሮ ብር 3,342,685.80 ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፣
2. በዩኒቨርስቲው የተለያዩ ኮሌጆች ውስጥ በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን የመኖሪያ ቤት እንደተሰጣቸው እየታወቀ በድምሩ ብር 880,800.00 የቤት ኪራይ አበል አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፣
3. ለግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ፣ ም/ስራ አስኪያጅ እና በጽ/ቤቱ ሥር ለሚገኙ ባለሙያዎች በየወሩ ብር 4000.00 የቶፕአፕ ክፍያ እንዲከፈላቸው የዩኒቨርሰቲው ስራ አመራር በወሰነው መሰረት ለአምስት ባለሙያዎች ከሀምሌ/2008 እስክ ሰኔ 30/2009 በድምሩ ብር

233,599.96 ከደንብና መመሪ ውጪ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ክፍያው ከመመሪያ ውጭ በመሆኑ እንዲቋረጥ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው አስተያየቱን ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

4. በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ኮሌጆች በአስተዳደር ቦታዎች (የሥራ መደቦች) ላይ የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በተደራቢነት በመመደብ በስራ አመራር ውሳኔ መሠረት የአንዋላይዜሽን እና የኃላፊነት አበል በድምሩ ብር 973,595.00 የተከፈለ መሆኑ፤
5. ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 844,321.52 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤
6. የተለያዩ ፈርኒቸሮች፤ የእቃ መደርደርያ ሽልፍና የእጅ ጋሪዎች በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ውሳኔ በብር 5,641,432.59 ያለውድድር በቀጥታ ግዢ የተፈጸመ መሆኑ፤
7. በተገቢው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ ብር 59,534.26 የወጪ ሂሣብ የተገኘ መሆኑ፤
8. ዩኒቨርሲቲው ከGIZ ጋር በገባው ውል መሰረት ለመሰረተ-ልማት ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ገዝቶ ለተወራረደው ብር 1,662,342.75 ዕቃው ገቢ ስለመደረጉ የሚያመለክት ማስረጃ፣ የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) እና ተ.እ.ታ (VAT) ስለመቆረጡ የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
9. ለምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር 30,000.00 እና ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ተቋም ብር 100,000.00 በድምሩ 130,000.00 መንግስታዊ ለሆኑ መ/ቤቶች ከመመሪያ ውጭ ለድጋፍ በሚል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
10. በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 464,232.84 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤
11. ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር ከመደበኛ በጀት በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ብር 362,732.84 ከተደለደው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤

1. ለዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር ከመደበኛ በጀት በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ብር 3,541,998.85 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች፤

1. የአስተዳደር ዘርፍ የሥራ መደቦች በሙሉ የሥራ ጊዜ የሚከናወኑ ሥራዎች እንደመሆናቸው ተገቢውን የሰው ሀይል መመደብ ሲገባ የህግ አገልግሎት ዳይሬክተር፤ የግንባታ ጽ/ቤት ዳይሬክተር፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፤ የቤተ መፅሐፍ እና ዶክመንቴሽን ዳይሬክተር፣ የስነ ምግባር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የፍሳሽ ማስወገድና ትሪትምንት ፕላንት ስራ አስኪያጅ፣ የሴቶች ጉዳይ እና ኤች አይ ቪ መከላከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የአዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ማዕከል ዳይሬክተር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር፣ የትብብርና አጋርነት ዳይሬክተር እና የቅሬታ ሰሚ ኦፊሰር የአካዳሚክ ባለሙያዎች (መምህራን) ሆነው በተጠቀሱት የሥራ መደቦች ላይ በተደራቢነት በኃላፊነት እያገለገሉ የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች በመከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈፀሙን፣ የተገዙ ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውንና እንዲሁም ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1.1 <u>ደመወዝና ጥቅማጥቅም፤</u>

1.1.1.1 <u>ግኝት፡ ለህክምና ባለሙያዎች ስለተፈጸመው ክፍያ፤</u>

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 እንደተደነገገው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ልዩ የሥራ ባሕሪ መሠረት በማድረግ ልዩ ልዩ የደመወዝ ስኬሎች እንዲጠኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድ ኤጀንሲው አጥንቶ ለምክር ቤቱ ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል ይላል ፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/71/390 በቀን10/18/8/03 በጻፈው ደብዳቤ የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች ደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመሆኑ በቦርድ ወይም በማኔጅመንት የሚወሰንና የሚከፈል ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በህክምና ትምህርት ኮሌጅ** ለጠቅላላ እና እስፔሻሊስት ሀኪሞች የቶፕአፕና ክሊኒካል አበል ክፍያ (Top-up and clinical allowance) በወር 40 ሰዓት ለጠቅላላ ሀኪሞች፤ በወር 120 ሰዓት ለስፔሻሊስቶች እንዲከፈላቸው በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በተወሰነው መሰረት ከሃምሌ/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 እና በ2008 በጀት ዓመት ያልተከፈለውን

ጨምሮ ብር 3,342,685.80 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 1** ተመልክቷል፡፡

1.1.1.2 **ስጋት፤**

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ካልተፈጸሙ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ ክፍያው ሊቋረጥ ይገባል፡፡ ክፍያዎች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪዎች መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

ክፍያው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሰረት፣ እንዲሁም የሌሎችን ዩኒቨርስቲዎች ተሞክሮ በመውሰድ የህክምና ትምህርት ለሚሰጡት እስፔሻሊስቶች የሚከፈል ክፍያ መሆኑን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በመወሰን በወር 40 ሰዓት ለጠቅላላ ሀኪሞች፤ በወር 120 ሰዓት ለስፔሻሊስቶች የተከፈለ ህጋዊ ክፍያ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1.1.1.5 **የኦዲተሩ አስተያየት፤**

የመንግሥት ሠራተኞች ጥቅማጥቅም የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመሆኑ ለጤና ባለሙያዎች የሚከፈለው የቶፕአፕና ክሊኒካል አሎዋንስ ክፍያ መቋረጥ ይኖርበታል፡፡

1.1.2.1 **ግኝት፣ ለቤት ኪራይና ለእንግዳ መምህራን ስለተፈጸመው ክፍያ**

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤት ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዩኒቨርሰቲው በተለያዩ ኮሌጆች ውስጥ በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን የመኖሪያ ቤት እንደተሰጣቸው እየታወቀ **በህክምና ትምህርት ቤት** ከሃምሌ እስከ የካቲት ብር 36,200፣ **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ** ከሃምሌ እስከ የካቲት ብር 75,200.00፣ **በህግ ትምህርት ቤት** ከሃምሌ እስከ የካቲት 144,000.00፣ **በስነ ትምህርትና ስነባህሪ ተቋም** ከሃምሌ እስከ መጋቢት ብር 63,000.00፣ **በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ** ከሃምሌ እስከ የካቲት ብር 180,800.00፣ **በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ** ከሃምሌ እስከ የካቲት ብር 46,800.00፣ **በቴክኖሎጂ ኮሌጅ** ከየካቲት እና መጋቢት ብር 31,200.00፣ **በግብርናና ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ** ከሃምሌ እስከ መጋቢት ብር 115,200.00፤ **በተፈጥሮ ሳይንስና ኮምፒዩቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ** ከሃምሌ እስከ የካቲት ብር 62,400.00፤ **በቡሬ ግቢ** ከሃምሌ እስከ ሚያዚያ ብር 126,000.00 በድምሩ ብር 880,800.00 ከደንብና መመሪያ ውጭ የቤት ኪራይ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 2** ተመልክቷል፡፡

1.1.2.2 **ስጋት፤**

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ካልተፈጸሙ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.1.2.3 **የማሻሻያሀሳብ፤**

ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈሉ ክፍያዎች ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡ እንዲሁም ክፍያዎች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪዎች መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.2.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

ዩኒቨርስቲው የአካባቢውን የቤት ኪራይ ዋጋ በማስጠናት እና በተጠናው ጥናት ዋጋ በመተመን ከመምህራኑ በተመጣጣን ዋጋ የቤት ኪራይ ያስከፍል የነበረ ሲሆን መኖሪያ ቤት አየተሰጣቸው ድጋሚ ከደመወዝ ጋር የቤት አበል የሚከፈላቸው የቤት አበል በጥሬ ገንዘብ የሚከፍሉትን በማቋረጥ ከኦዲት ግኝት በኂላ ከደመወዝ ጋር የሚከፈለው የቤት አበል እንዲቆም ተደርጓል፡፡

1.1.3.1 ግኝት፣ አለአግባብ የተከፈለ የቶፕ አፕ፤ የአኑዋላዜሽንና የኃላፊነት ክፍያ፤

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 እንደተደነገገው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ልዩ የሥራ ባሕሪ መሠረት በማድረግ ልዩ ልዩ የደመወዝ ስኬሎች እንዲጠኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድ ኤጀንሲው አጥንቶ ለምክር ቤቱ ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል ይላል ። በተጨማሪም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/71/390 በቀን10/18/8/03 በጻፈው ደብዳቤ የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች ደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመሆኑ በቦርድ ወይም በማኔጅመንት የሚወሰንና የሚከፈል ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው ተገልጿል። ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በዋናው ግቢ** ለግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ፤ ም/ስራ አስኪያጅ እና በጽ/ቤቱ ስር ለሚገኙ ባለሙያዎች የቶፕ አፕ ክፍያ በየወሩ ብር 4000.00 እንዲከፈል የዩኒቨርስቲው ስራ አመራር በቀን 22/06/2008 በቁጥር ፐ/5966/08/08 በወሰነው መሰረት ለአምስት ባለሙያዎች ከሀምሌ/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 በድምሩ ብር 233,599.96 አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል። በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ክፍያው ከመመሪያ ውጭ በመሆኑ እንዲቋረጥ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው አስተያየቱን ተግባራዊ አላደረገም።
- **በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ኮሌጆች** በአስተዳደር ቦታዎች (የሥራ መደቦች) ላይ የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በተደራቢነት በመመደብ በስራ አመራር ውሳኔ መሠረት የአንዋላይዜሽን እና የኃላፊነት አበል በድምሩ ብር 973,595.00 ተከፍሎ ተገኝቷል። ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 3** ተመልክቷል።

1.1.3.2 ስጋት፤

ክፍያዎች በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ካልተፈጸሙ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

1.1.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ መፈጸም አግባብ ባለመሆኑ ክፍያው ሊቋረጥ ይገባል። ክፍያዎች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪዎች መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል።

1.1.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- ዩኒቨርስቲው እያስገነባ ያለው የግንባታ ፕሮጀክት ከ1 ቢሊዩን ብር በላይ ሲሆን በመዋቅር የተፈቀደው የስራ መደብ ላይ በማስታወቂያ ተፈልጎ በገበያው ላይ በተፈቀደው በጀትና ስራ ልምድ መሃንዲሶችን ማግኘት ባለመቻሉ ለስራ መደቡ የተፈቀደውን በጀት እና ባለሙያዎቹ የሚከፈላቸውን የደመወዝ ልዩነት በማኔጅመንት በመወሰን በቶፐአፕ መልኩ እንዲከፈል ጊዜያዊ መፍትሄ በማድረግ ግንባታዎች ያለምንም መቆራረጥ በጥራት እንዲሰሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ መሆኑን እየገለፅን አሁንም በስራ መደቡ ላይ መሃንዲሶች የሚገኙ ከሆነ ፍለጋችን ያለማቋረጥ የምንቀጥል መሆኑ እንዲታወቅ፣
- ለስራው አስፈላጊና በትምህርት የሰለጠኑበት ስለሆነ ስራውን በውክልና ለመመህራን ሲሰጥ የግድ ጥቅማጥቅም መከፈል ስለነበረበት በአስተዳደር ካውንስል ውሳኔ መሰረት የተከፈለ ክፍያ ነው፡፡

1.2. የዕቃና አቅርቦቶች ክፍያዎች፤

1.2.1.1 ግኝት፣ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረደ ግዢ ክፍያ፤

በፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው የመንግስት መ/ቤቶች ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጭዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሠረት ለግዥ ክፍያዎች ተገቢው ደረሰኝ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተለያዩ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዢ ለተለያዩ አቅራቢዎች (ድርጅቶች) ተከፍሎ በወጪ ለተመዘገበው ብር 844,321.52 የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	የትምህርት ክፍል/ኮሌጅ	የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ/ የክፍያ ማዘዣ	ገንዘቡ የተከፈለው ድርጅት	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	ዋናው ግቢ	891570	አንበሣ ጫማ	ለጫማ ግዢ	612,169.48
2	››	888970	አባድር ሾፒንግ	ለሳሙና ግዢ	43,336.55
3	››	1004065	ኢትዮ ኒፓን	ለተሽከርካሪ ሰርቪስ	99,742.12
4	ጤና ሳይንስ	891273	የመድሃኒት ፈንድ አቅርቦት ኤጀንሲ	ለመደኃኒት ግዢ	89,073.37
				ድምር	**844,321.52**

1.2.1.2 ስጋት፣

በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የወጪ ሂሳብ እንዲመዘገብ ማድረግ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ ሲቀርብ ሂሣቡ በድጋሚ በወጪ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

1.2.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በዱቤ ሽያጭ ለተመዘገበው የወጪ ሂሳብ የገንዘብ ክፍያ ደረሰኝ እንዲቀርብ እንዲደረግና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የመንግስት የግዥ ኤጀንሲ የሚገዛቸው ዕቃዎች በእኛ በኩል ንብረቱ ገቢ መደረጉን፣ የቀረበውን ደረሰኝ ውሉን፣ ቅድመ-ግብር እና የተጨማሪ አሴት ታክስ በመቀነስ ድርጅቱ ባሳወቀው የባንክ አካውንት ቁጥር ገንዘቡን ገቢ ለማድረጋችን የባንክ አድቫይስ ከሂሳቡ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ትክክል አሰራር ሲሆን ለወደፊቱ ድርጅቱ የሽያጭ የገቢ ደረሰኝ እንዲልክልን በማድረግ ለተጨማሪ መረጃ ከሂሳቡ ጋር እንዲያያዝ እናደርጋለን፡፡

1.2.2.1 ግኝት፤ የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ምዝገባ፤

በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6ለ መሠረት የሂሣብ እንቅስቃሴ መነሻ ሠነድ የተዘጋጀላቸው ሂሣቦች በዕለቱ በፋይናንስ ምንጩ በሂሣብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሣብ ሌጀር ላይ መወራረስ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ የወጪ ሂሳቦች ነሃሴ 1999 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ (Chart of Accounts) መሠረት መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለዩኒቨርሲቲው የፅዳት አገልግሎት ለሰጡት ለእነትግስት፤ ወይንሸት እና ጓደኞችዋ የተከፈለው ብር 59,534.26 በ6251 (በውል ለሚፈፀም የሙያ አገልግሎት) ሂሳብ መደብ መመዝገብ ሲገባው በ6218 (በሌሎች አቅርቦቶች) ሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

1.2.2.2 ስጋት፣

በሂሳብ መደቡ ሪፖርት የተደረገው ሂሳብ በስራ ላይ የዋለውን ትክክለኛ ወጪ እንዳያሳይ

ከማድረጉም በተጨማሪ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

1.2.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የወጪ ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ እንዲመዘገብና ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በጥቃቅን አነስተኛ የተደራጁ አነትዕግስት፣ ወይንሸትና ጓደኞቹዋ የፅዳት እቃዎች በመግዛት የማፅዳት ስራ ስለሚሰሩ በሌሎች አቅርቦቶች የሂሳብ መደብ መከፈሉ አግባብነት ያለው ቢሆንም ለወደፊቱ በተሰጠው አስተያየት መሰረት በውል የሚፈፀም የሙያ አገልግሎት የሚከፈል በሚለው የሂሳብ መደብ በጀት በመያዝ እንዲከፈል እናደርጋለን፡

1.2.3.1 <u>ግኝት፣ ያለውድድር በቀጥታ የተፈጸመ ግዢ፤</u>

በፌዴራል የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ምዕራፍ 6 አንቀጽ 52 ተራ ቁጥር አንድ ላይ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት በፊደል ‹‹ሀ›› ዕቃው፤ የግንባታ ዘርፍ ሥራው፤ የምክር ወይም ተፈላጊው ሌላ አገልግሎት የሚገኘው ከአንድ ዕጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 888783 የተለያዩ ፈርኒቸሮች፤ የእቃ መደርደርያ ሽልፍና የእጅ ጋሪዎች በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ውሳኔ ከመከላከያ ግንባታ ግብአቶች ማምረቻ ድርጅት (ቃሊቲ ኮንስትራክሽን እቃዎች ማምረቻ ፋብሪካ) በብር 5,641,432.59 በቀጥታ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

1.2.3.2 <u>ስጋት፣</u>

ግዢዎች በደንብና መመሪያ መሠረት ካልተፈጸሙ ዩኒቨርሲቲው በውድድር ማግኘት የሚችለውን ጥቅም እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

1.2.3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ግዢዎች በደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ ማድረግ ይገባል፡፡

1.2.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ግኘው የተፈፀመው መንግስታዊ የልማት ድርጅት በመሆኑ የስራ አመራሩ ዋጋ በመጠየቅና የገበያውን ዋጋ በማስጠናት አዋጪ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት በቀጥታ ግዥው እንዲፈም የተደረገ ሲሆን ለወደፊቱ ከመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በማስፈቀድ ለመፈፀም ጥረት ይደረጋል፡፡

1.3 ለቋሚ ዕቃዎችና መሠረተ-ልማት ሥራዎች ክፍያ፤

1.3.1.1 ግኝት፤ የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት የግንባታ ሥራ ክፍያ፤

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የፋይናንስ ኃላፊነት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች ቁጥር 6(ለ) የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ሥራዎች ክፍያ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ24/04/09 በሂሳብ መዝገብ ማዘዣ ቁጥር 71583 በሂሳብ መደብ 6324 ዩኒቨርሲቲው ከGIZ ጋር በገባው ውል መሰረት ለመሰረት ልማት ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች ከተለያዩ ድርጅቶች ገዝቶ ለተወራረደው ብር 1,662,342.75 ዕቃው ገቢ ስለመደረጉ የሚያመለክት ማስረጃ፣ የቅድመ ግብር ክፍያ (withholding tax) እና ተ.እ.ታ (VAT) ስለመቆረጡ የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

1.3.1.2 ስጋት

የተሟላ የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብና ክፍያ መፈፀም የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

1.3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

ለክፍያዎች የተሟላ ተገቢ ማስረጃ እንዲቀርብ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

GIZን በተመለከተ ክፍያ የሚፈፅመው በመ/ቤቱ በኩል ነው፤ ዩኒቨርስቲው ሂሳብን የሚያወራርደው በሚቀርብለት ክፍያ ነው፤ ዕቃዎች ገቢ የሚደረጉት በGIZ በኩል በመሆኑ ማስረጃው የሚገኘው እዛው ነው፡፡

1.4 ሌሎች ክፍያዎች

1.4.1.1 ግኝት፤ የድጋፍ ክፍያን በሚመለከት፤

ነሃሴ 1999 የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በወጣው የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት መመሪያ መሠረት በ6412 የሂሳብ መደብ የሚያዙ ሂሳቦች ነፃ የአስተዳደር አቋም ላላቸው ተቋሞች እንዲሁም መንግስታዊ ላልሆኑ የማህበራዊ፣ የሀይማኖት እና የባህል ድርጅቶች የሚሰጥ የገንዘብ እርዳታ መሆኑ በተደነገገው መሠረት ወጪዎችን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

- በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 883038 ለምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር 30,000.00 እና በባንክ ወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር 887171 ለኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ተቋም ብር 100,000.00 በድምሩ 130,000.00 መንግስታዊ ለሆኑ መ/ቤቶች ከመመሪያ ውጭ ለድጋፍ በሚል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.4.1.2 ስጋት

የፋይናንስ ደንብና መመሪያን መሰረት ያላደረገ ክፍያ መፈጸም የመንግስትን ሀብት ለብክነት ሊያጋለጥ ይችላል፡፡

1.4.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ክፍያዎች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪዎች መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡

1.4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የዩኒቨርስቲው የሥራ አመራር በወሰነው ውሳኔ ከድጋፍ በጀት የተከፈለ ሲሆን ከገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር እንዳይከፈል መመሪያ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲቆም ተደርጓል፡፡

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

2.1 <u>ግኝት፤</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ "ለ" የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ቢያመለክትም፤ በሰኔ 30/2009 በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ሂሳብ በድምሩ ብር 464,232.84 በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

- በሂሳብ መደብ 4201 (ልዩ ልዩ ቅድመ ክፍያዎች) ለተለያዩ ግለሰቦች ከ1995 እስከ 2009 ተሰጥቶ በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 382,503.02 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4211 (ለግዢ ሠራተኞች ቅድመ ክፍያ) ለግዥ ሰራተኞች ከ1995 እስከ 2009 ተሰጥቶ በወቅቱ ያልተወራረደ ብር 81,729.82 የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2 <u>ስጋት፤</u>

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ተሰብሳቢ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.4 <u>የሚመለከተው ኃላፊ ምላሽ፤</u>

- በ4201 ለምርምር የወስዱት ሲሆን ጌዜው ሲደረስ የሚወራረድ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች እየተጣሩ በህግ የሚጠይቁ ይሆናል፡፡
- በ4211 በግዥ ሰራተኞች የሚታየው ሂሳብ በወቅቱ ባለመወራረዱ የታየ ሂሳብ ነው፡፡

3. <u>በጀት፣</u>

3.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የተፈቀደው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የበጀት ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀት እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር ከመደበኛ በጀት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት ብር 3,541,998.85 ሳይሰራበት ተራፊ ሆኖ የተገኘ ሲሆን ብር 362,732.84 ደግሞ ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 4** ተመልክቷል፡፡

3.2 <u>ስጋት፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የታወጀለትን በጀት በወቅቱ አለመጠቀሙ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም በላይ የሀገሪቱን ውስን ሃብት ያለጥቅም እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ከበጀት በላይ መጠቀም ደግሞ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

3.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል እና ከተፈቀደዉ በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

4.1.1 <u>ግኝት፣ በአስተዳደር ስራ ላይ ስለተሰማሩ መምህራን በተመለከተ፤</u>

የአስተዳደር ዘርፍ የሥራ መደቦች በሙሉ የሥራ ጊዜ የሚከናወኑ ሥራዎች እንደመሆናቸው ተገቢውን የሰው ሀይል መመደብ ሲገባ በዩኒቨርሰቲው የህግ አገልግሎት ዳይሬክተር፤ የግንባታ ጽ/ቤት ዳይሬክተር፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፤ የቤተ መፅሐፍ እና ዶክመንቴሽን ዳይሬክተር፣ የስነ ምግባር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የፍሳሽ ማስወገድና

ትሪትምንት ፕላንት ስራ አስኪያጅ፣ የሴቶች ጉዳይ እና ኤች አይ ቪ መከላከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ የአዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ማዕከል ዳይሬክተር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር፣ የትብብርና አጋርነት ዳይሬክተር እና የቅሬታ ሰሚ ኦፊሰር የአካዳሚክ ባለሙያዎች (መምህራን) ሆነው በተጠቀሱት የሥራ መደቦች ላይ በተደራቢነት በኃላፊነት እያገለገሉ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.1.2 ስጋት፣

ቋሚ የአስተዳደር የስራ መደቦች በአካዳሚክ ባለሙያ (በመምህራን) በተደራቢነት እንዲያዙ ማድረግ የየክፍሎቹ ሥራዎች በወቅቱና በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዳይከናወኑ ያደርጋል፡፡

4.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

በቋሚ የአስተዳደር የስራ መደቦች ላይ በተደራቢነት ተመድበው የሚሰሩ የአካዳሚክ (መምህራን) ምደባ መመሪያውን ያልተከተለ በመሆኑ የሰራተኞች ምደባ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት መፈጸም ይኖርበታል፡፡

4.2.1 ግኝት፣ የስጋት ተጋላጭነትን በተመለከተ፤

በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች አይነት ቁጥር 6 አጠቃላይ ደረጃዎች ንዑስ ቁጥር 5 የሥራ አመራሩ በስጋት ተጋላጭነት ላይ ተገቢ እና ተስማሚ እርምጃ መውሰድ እንዲችል በመ/ቤቱ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ላይ የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ በየጊዜው መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- የስጋት ምንጮች ዳሰሳ ያልተደረገና ዩኒቨርሲቲው በፖሊሲ ደረጃ የስጋት ተጋላጭነት (Risk policy management) የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

4.2.2 ስጋት፣

የስጋት አካባቢዎች ተለይተው ችግሮች ሲገጥሙ የሚፈቱበት አቅጣጫ ካልተቀመጠ የታቀዱ ተግባራትን ለማሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በአግባቡና በወቅቱ ለማስተካከል አያስችልም፡፡

4.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ዩኒቨርሲቲው የስጋት ምንጮች የሆኑትን አካባቢዎችና ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችና የተጋላጭነት ደረጃ በመለየት በመመሪያው መሰረት ሊሰራ ይገባል፡፡ ይኸውም በንብረት አመዘጋገብና አጠባበቅ፣ በገቢ አሰባሰብ፣ በወጪ አስተዳደር፣ በግዥ አፈጻጸም፣ በሰው ሀብት አስተዳደር፣ በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በመረጃ ግንኙነት ስርዓት፣ በተሽከርካሪዎች አጠቃቀምና አጠባበቅ ዙሪያ ትኩረት ተሰጥቶ መስራት ይገባል፡፡

5. በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች በተመለከተ፣

5.1 ግኝት፣

የፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 አንቀጽ 10ለ እና 10ሐ ሂሣብ ኦዲት ማስደረግን በሚለው ስር «በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት በወቅቱ የእርምት እርምጃዎችን የመውሰድና፣ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና የኦዲት ሪፖርት ላቀረበው አካል የማሳወቅ ኃላፊነት እንዳለበት» መመሪያው ይገልጻል፡፡ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው በ2007 እና 2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ከዚህ በታች በተገለጹ ዋና ዋና ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡

በ2008 በጀት ዓመት የተገኙ ግኝቶች፣

- ለሐኪሞች ለማበረታቻ (ቶፕ አፕ) የደመወዛቸው 50% እና የህክምና የሙያ አበል ብር 800.00 እንዲሁም ለስፔሻሊስቶች ለማበረታቻ (ቶፕ አፕ) የደመወዛቸው 50% እና የሙያ አበል ብር 2,000.00 በወር እንዲከፈላቸው የስራ አመራር ቦርድ በ19/08/2007 ባስተላለፈው ውሳኔ መሰረት እየተፈጸመ የሚገኘው ክፍያ እንዲቋረጥ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ያልተቋረጠ መሆኑ፣
- ግንባታዎችን ክትትል ለሚያደርጉ የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ባለሙያዎች የትርፍ ሰዓትና የማበረታቻ (ቶፕአፕ) ክፍያ በሚል የሚፈጸመው ክፍያ እንዲቋረጥ አስተያየት ቢሰጥም ያልተቋረጠ መሆኑ፣
- GIZ-IS ትምህርት ሚኒስቴር ባሳተመው ደረሰኝ ከኮንትራክተር የሰበሰበውን ብር 682,243.73 ተጨማሪ እሴት ታክስ ወደ ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ለማድረጉ ማስረጃ ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፣

- በዩኒቨርሲቲው ምን ያህል ህንጻዎች እንዳሉ፤ ህንጻዎች ከህንጻ ስራ ተቋራጮች በንብረትነት ተረክቦ ገቢ ያልተደረጉና የተሟላ ዝርዝር የህንጻዎችን ታሪክ የሚያስረዳ ምዝገባ የሌለ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው በአስተዳደር የስራ መደቦች በዳይሬክተር ደረጃ (ፕሳ 9) የሚመደቡ ኃላፊዎችን በአዋጁ በተገለጸው እና በፐብሊክ ሰርቪስና በሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር በጸደቀው መዋቅር መሰረት የስራ መደቡን የሚያሟሉትን ሰራተኞች አወዳድሮ ምደባውን ማከናወን ሲገባ 7 ቁልፍ የዳይሬክተር የስራ መደቦች ያለተፈላጊ ችሎታና ያለውድድር በመምህራን መያዛቸው፣

<u>በ2007 በጀት ዓመት የተገኙ ግኝቶች፤</u>

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ብር 11,217.53 በማነስ የታየ መሆኑ፣
- ብር 747,574.31 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላግባብ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ሶስት የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የኮምፒውተርና የቢሮ መገልገያዎችን ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ፣

5.2 <u>ስጋት</u> ፣

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

5.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪ ቁጥር 1. ለጠቅላላና ስፔሻሊስት ሐኪሞች የተከፈለ ቶፕአፕና ክሊኒካል አሎዋንስ

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ አይነት	የደረሰኝ ቁጥር	የመምህራን ብዛት	ወር	የገንዘቡ ልክ
1	08/07/2009	Jv	1006530	ለ28 ዶክተሮች	ሰኔና ሐምሌ/2008	368,883.00
2	06/03/2009	Jv	1006232	ለ28 ዶክተሮች	መስከረም	202,166.33
3	20/01/2009	Jv	1006215	ለ28 ዶክተሮች	ሐምሌና ነሐሴ	98,980.00
4	15/03/2009	Jv	1006234	ለ28 ዶክተሮች	ጥቅምት	205,385.00
5	06/04/2009	Jv	1006246	ለ28 ዶክተሮች	ህዳር	244,501.35
6	06/06/2009	Jv	1006520	ለ36 ዶክተሮች	ጥር	278,521.66
7	17/05/2009	Jv	1006509	ለ37 ዶክተሮች	ታህሳስ	332,185.66
8	03/09/2009	Jv	1007902	ለ38 ዶክተሮች	የካቲት መጋቢት ወር	315,321.97
9	16/10/2009	Jv	1007923	ለ44 ዶክተሮች	የካቲት፤ መጋቢት፤ሚያዚያና ግንቦት	958,940.83
10	03/09/2009	Jv	1007935	ለ45 ዶክተሮች	ሰኔ	337,800.00
					ድምር	**3,342,685.80**

አባሪ ቁጥር 2. የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን አላግባብ የተከፈለ የቤት ኪራይ ክፍያ

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ አይነት	የደረሰኝ ቁጥር	ወር	የገንዘብ መጠን
	የህክምና ትምህርት				
1	29/11/2008	JV	1006201	ሀምሌ	6,200.00
2	27/12/2008	JV	1006209	ነሀሴ	6,200.00
3	27/01/2009	JV	1006216	መስከረም	3,200.00
4	28/02/2009	JV	1006227	ጥቅምት	3,200.00
5	26/03/2009	JV	1006237	ህዳር	5,200.00
6	20/04/2009	JV	1006249	ታህሳስ	4,200.00
7	29/05/2009	JV	1006510	ጥር	4,400.00
8	22/06/2009	JV	1006522	የካቲት	3,600.00
				ንዑስ ድምር	**36,200.00**
	ጤና ሳይንስ ኮሌጅ				
1	28/11/2008	JV	1004701	ሀምሌ	9,400.00
2	26/12/2008	JV	1004704	ነሀሴ	9,400.00
3	26/01/2009	JV	1004713	መስከረም	9,400.00
4	25/02/2009	JV	1004719	ጥቅምት	9,400.00
5	26/03/2009	JV	1004729	ህዳር	9,400.00
6	25/04/2009	JV	1004740	ታህሳስ	9,400.00
7	22/05/2009	JV	1006302	ጥር	9,400.00
8	22/06/2009	JV	1006312	የካቲት	9,400.00
				ንዑስ ድምር	**75,200.00**
	የህግ ት/ቤት				
1	26/11/2008	JV	1004560	ሀምሌ	16,200.00
2	25/12/2008	JV	1004564	ነሀሴ	16,200.00
3	23/01/2009	JV	1004567	መስከረም	18,600.00
4	22/02/2009	JV	1004573	ጥቅምት	18,600.00
5	20/03/2009	JV	1004574	ህዳር	18,600.00
6	20/04/2009	JV	1004578	ታህሳስ	18,600.00
7	19/05/2009	JV	1004585	ጥር	18,600.00
8	24/06/2009	JV	1004589	የካቲት	18,600.00
				ንዑስ ድምር	**144,000.00**
	የስነ ትምህርትና ስነ ባህሪ ተቋም				
1	29/11/2008	PV	880577	ሀምሌ	7,000.00
2	27/12/2008	PV	880585	ነሀሴ	7,000.00

3	27/01/2009	PV	880598	መስከረም	7,000.00
4	29/02/2009	PV	883259	ጥቅምት	7,000.00
5	30/03/2009	PV	883274	ህዳር	7,000.00
6	26/04/2009	PV	883282	ታህሳስ	7,000.00
7	29/05/2009	PV	883296	ጥር	7,000.00
8	28/06/2009	PV	886251	የካቲት	7,000.00
9	29/07/2009	PV	886259	መጋቢት	7,000.00
				ንዑስ ድምር	**63,000.00**
	ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ				
1	28/11/2008	JV	1005483	ሀምሌ	22,600.00
2	27/12/2008	JV	1005491	ነሀሴ	22,600.00
3	25/01/2009	JV	1005493	መስከረም	22,600.00
4	28/02/2009	JV	1005498	ጥቅምት	22,600.00
5	24/03/2009	JV	1005505	ህዳር	22,600.00
6	20/04/2009	JV	1005507	ታህሳስ	22,600.00
7	24/05/2009	JV	1005510	ጥር	22,600.00
8	24/06/2009	JV	1005516	የካቲት	22,600.00
				ንዑስ ድምር	**180,800.00**
	ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጂ				
1	26/05/2009	JV	1004937	ጥር	23,400.00
2	28/08/2009	JV	1004946	የካቲት	23,400.00
				ንዑስ ድምር	**46,800.00**
	ቴክኖሎጂ ኮሌጅ				
1	22/06/2009	JV	1006835	የካቲት	15,600.00
2	19/07/2009	JV	1007705	መጋቢት	15,600.00
				ንዑስ ድምር	**31,200.00**
	ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ				
1	27/11/2008	JV	1005788	ሀምሌ	12,800.00
2	23/12/2008	JV	1005792	ነሀሴ	12,800.00
3	24/01/2009	JV	1005798	መስከረም	12,800.00
4	22/02/2009	JV	1006001	ጥቅምት	12,800.00
5	21/03/2009	JV	1006002	ህዳር	12,800.00
6	20/04/2009	JV	1006014	ታህሳስ	12,800.00
7	18/05/2009	JV	1006018	ጥር	12,800.00
8	21/06/2009	JV	1006022	የካቲት	12,800.00
9	22/07/2009	JV	1006029	መጋቢት	12,800.00
				ንዑስ ድምር	**115,200.00**

	የተፈጥሮና ኮምፒቴሽናል ሳይንስ ኮሌጅ				
1	29/11/2008	PV	880520	ሀምሌ	7,800.00
2	26/12/2008	PV	880529	ነሀሴ	7,800.00
3	24/01/2009	PV	943919	መስከረም	7,800.00
4	25/02/2009	PV	943931	ጥቅምት	7,800.00
5	26/03/2009	PV	943936	ህዳር	7,800.00
6	/04/2009	PV	943942	ታህሳስ	7,800.00
7	/05/2009	PV	943947	ጥር	7,800.00
8	/06/2009	JV	1006555	የካቲት	7,800.00
				ንዑስ ድምር	**62,400.00**
	ቡሬ ካምፓስ				
1	27/11/2008	PV	71474	ሀምሌ	12,600.00
2	25/12/2008	PV	71478	ነሀሴ	12,600.00
3	24/01/2009	PV	71485	መስከረም	12,600.00
4	24/02/2009	PV	71495	ጥቅምት	12,600.00
5	22/03/2009	JV	1005562	ህዳር	12,600.00
6	26/04/2009	JV	1005574	ታህሳስ	12,600.00
7	24/05/2009	JV	1005591	ጥር	12,600.00
8	21/06/2009	JV	1005596	የካቲት	12,600.00
9	22/07/2009	JV	1005506	መጋቢት	12,600.00
10	20/08/2009	JV	1005615	ሚያዝያ	12,600.00
				ንዑስ ድምር	**126,000.00**
				ጠቅላላ ድምር	**880,800.00**

አባሪ ቁጥር 3. አላግባብ የተከፈለ የአኑዋላዜሽንና የኃላፊነት ክፍያ፤

ተ.ቁ	የትምህርት ክፍል/ኮሌጅ	የተከፈለው የሥራ ኃላፊ	የክፍያው ጊዜ (ከ-እስከ)	ወርሃዊ የአኑዋላዜሽን ክፍያ	ወርሃዊ የኃላፊነት አበል ክፍያ	በዓመቱ የተከፈለ ድምር
1	ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ	ለማህበረስብ አገልግሎት ኦፊሰር	ከሃምሌ/2008 - ሰኔ/2009	2,094.00	750.00	34,128.00
2	›› ››	የጮቁ/ተ/የም/ል/ፐ/ዳይሬክተር	›› ››	2,628.00	1,500.00	37,217.00
3	›› ››	የግቢ ውበት ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	35,515.00
4	›› ››	የም/ማ/ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	19,501.00
5	›› ››	የተማሪዎች አገልግሎት ም/ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,000.00	37,128.00
6	ሶሻል ሣይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ	ለአዲስ አለማየሁ የባህልና ጥናት ተ/ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
7	›› ››	የአ/አለ/መዛ/ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	34,128.00
8	›› ››	የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር	›› ››	2,628.00	1,500.00	49,536.00
9	›› ››	ELIC አስተባባሪ	›› ››	2,094.00	900.00	29,940.00
10	›› ››	የስ/ያ/ኤአይቪ/አካ/ጉ/ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	35,628.00
11	›› ››	የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያ ኃላፊ	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
12	›› ››	የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	7,188.00
13	›› ››	የቅሬታ ሰሚ ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	34,128.00
14	›› ››	የሰው ሀብት ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	23,658.00
15	ተፈጥሮና ኮሚፐቴሽናል ኮሌጅ	የተማሪዎች አገልግሎት ዳሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
16	›› ››	የተቋማዊ ለውጥ	›› ››	2,628.00	1,500.00	43,128.00
17	›› ››	የስልጠናና ማማከር ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	34,128.00
18	›› ››	የውስጥ ጥራት ቁጥጥር	›› ››	2,094.00	750.00	34,128.00
19	ህግ ትምህርት	ለፕሬዘዳንት ጽ/ቤት	›› ››	2,628.00	1,500.00	49,536.00
20	›› ››	የህግ አገልግሎት ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
21	›› ››	የስነ-ምግባር ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
22	ቴክኖሎጂ ኮሌጅ	ለUIL ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	34,128.00
23	›› ››	የቴ/ሽ/ኦፊሰር	›› ››	2,094.00	750.00	34,128.00
24	›› ››	የግንባታ ቁጥጥር ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
25	›› ››	የላይብረሪ መሪ/ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
26	›› ››	የICT ዳይሬክተር	›› ››	2,094.00	1,500.00	43,128.00
27	›› ››	የትሪትመንት ፕላንት ስራ አስኪያጅ	›› ››	1,662.00	750.00	21,700.00
					ድምር	**973,595.00**

አባሪ ቁጥር 4. የ2009 በጀት ዓመት በጀት ማመዛዘኛ

የወጪ የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ስራ ላይ የዋለ ወጪ	ያልተሰራበት በጀት	ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገ	ልዩነት %
መደበኛ በጀት					
6116	25,861,832.00	26,224,566.84		362,732.84	1.40
6211	3,459,205.00	2,193,022.21	1,266,182.79		36.6
6214	1,250,840.00	980,392.62	270,447.38		21.6
6218	2,085,600.00	1,787,916.21	297,683.79		14.3
6219	299,300.00	246,550.21	52,749.79		17.6
6221	29,050.00	13,338.11	15,711.89		54.1
6232	2,400,500.00	1,857,287.25	543,212.75		22.6
6243	376,600.00	332,217.26	44,382.74		11.8
6255	275,500.00	108,081.24	167,418.76		60.7
6256	685,000.00	515,030.86	169,969.14		24.8
6259	254,674.00	182,013.54	72,660.46		28.5
6271	325,000.00	258,210.00	66,790.00		20.5
6417	900,200.00	325,410.64	574,789.36		63.8
ድምር	**38,203,301.00**	**35,024,036.99**	**3,541,998.85**	**362,732.84**	